# <u>ምልክት</u> ፡ አንድነት እና ያለ ፍርሀት መሆን ከመከራ ስጦታ ጋር

**ወደ ፊሊጵስዩስ ሰዎች ከ1፡27-30 ያለውን ማሰላሰል።**

<<ይሁን እንጂ፥መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ፥በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሀይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ፥ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እሰማ ዘንድ፥ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ። በአንድም ነገር እንኳን በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚያብሔር ነው፣ ይሀ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኃልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።>>

በቅርቡ ለሁለት ቀናት የተደረገው የመጋቢዎች የጸሎትና የእቅድ ስብሰባ ላይ የጠዋቱን የጸሎት ጊዜ የመራሁበት ቃል ነበር። የኔ አላማ ሶስት ነገሮችን ያቀፈ ሲሆን የመጀመሪያው እንደ መጋቢነታችን ክርስቶስን በማገልገል ውስጥ ያለ መከራ ጥሪያችን መሆኑን በጥልቀት ለማሳየት ፈልጌ ነው። በእርግጥ ይህ የእግዚያብሔር ሥጦታ ነው። ሁለተኛው፥ በወንጌል ምክንያት መከራን በአንድነትና ያለ ፍርሀት መቀበል ምልክት መሆኑን እንድናይ፤ እንዲሁም በሶስተኛ ደረጃ ስለ ክርስቶስ ወንጌል እና ስለ ሰዎች ስንል ትከሻዎቻችንን አንድ ላይ ለማድረግ እና ጎን ለጎን ለመስራት ራሳችንን ለማነሳሳት ነበር። እነዚህን ነገሮች ለማየት ከእኛ ጋር ይታደሙ።

በመጀመሪያ ክርስቶስን በማገልገል ውስጥ ያለ መከራ የእግዚያብሔር ሥጦታ እንዲሁም የመጋቢነታችን ጥሪም አካል ነው። በቁጥር 29 ላይ <<ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷችኋልና፤ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም>> የሚል ኃሳብ አለ። በዚህ ክፍል ላይ እምነትና መከራ የእግዚያብሔር ስጦታዎች እንደሆኑ ይናገራል፤<<መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም።>> ይህ የተነገረው ለተራ አማኞች ነው። ስለዚህም ለእኛ ለመጋቢዎች ሁሉ ይሰራል። እንደ ክርስቲያኖች ማመንና መከራን መቀበል በክርስቶስ አገልግሎት ውስጥ የጥሪያችን አካል ነው። ይበልጡን ደግሞ በመሪነት ባለን ጥሪ ውስጥ። በ 2 ቆሮንቶስ 1፡6 <<ዳሩ ግን መከራ ብንቀበል፥ ስለ መጽናናታችሁና ስለ መዳናችሁ ነው፤ ብንጽናናም፥ እኛ ደግሞ የምንሰቃይበት በዚያ ስቃይ በመጽናት ስለሚደረግ ስለ መጽናናታችሁ ነው>> ይላል። ያ እንድንመለከተው የፈለግሁት የመጀመሪያ ነገር ነበር። መከራ መቀበል ጥሪያችን፥ ከእግዚያብሔርም ዘንድ የተሰጠን ስጦታችን ነው። እርግማን አይደለም። ሥጦታ ነው።

ሁለተኛ ይህን መከራ በህብረት እና ያለ ፍርሀት ሥንቀበል÷ ምልክት ነው፡፡ ወደ ፊሊጵስዩስ ሰዎች 1፡27-28 ላይ የተጠቀሰውን የነዚህን ሰዎች አንድነት እና ያለ ፍርሀት መሆን እንመልከት፡፡ <<በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሀይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ…በአንድ ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ ይህም ለእነርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው÷ ይህም ከእግዚያብሔር ነው፡፡>> አንድነት "በአንድ ልብ" እና "መንፈስ" እንዲሁም "አብራችሁ እየተጋደላችሁ" በሚሉት ሀረጎች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡ ያለፍርሀት መሆን ደግሞ "በአንድም ነገር እንኳን…አትደንግጡ" በሚለው ሀረግ ውስጥ አጽንኦት ተሰጥቶታል፡፡ መከራን በመጋፈጥ ረገድ አንድነትንና ያለፍርሀት መሆን የሚለው እውነት ለመጀመሪያ ጊዜ የታየው "በተቃዋሚዎች" በሚለው ቃል ውስጥ ሲሆን÷ለሁለተኛ ጊዜ ድጋፍ ያገኘው "ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷችኃልና ስለ እርሱ መከራ ልትቀበሉ እንጂ" በሚለው ክፍል ላይ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በተቃዋሚዎቻችሁ ፊት÷ አንድ እና ያለፍርሀት ሁኑ፤ ምክንያቱም መከራችሁ የእግዚያብሔር ስጦታ ነውና፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ የተባለው ምልክት ነው፡፡ ማለትም በመከራ ጊዜ አንድነታችሁና ያለ መፍራታችሁ ለተቃዋሚዎቻችሁ የጥፋት÷ ለእናንተ ደግሞ የመዳን ምልክት ነው፡፡ ስለ ክርስቶስ በምትቀበሉት መከራ በአንድነታችሁና ባለ መፍራታችሁ÷ እውነቱና የክርስቶስ ክብር ይታያል፡፡ አንደ አገልጋይነታችንና እንደ ቤተ ክርስቲያን ይህ ትልቁ አላማችን ነው፡፡ የክርስቶስን ታላቅ የእውነትንና የዋጋ ምልክት በአለም ማንጸባረቅ ነው፡፡ የወንጌል ተቃዋሚዎች በሙሉ ሲጠፉ÷ ይህንን እውነት የተቀበሉት ግን ይድናሉ፡፡ በመጨረሻም÷ አገልጋዮችን በሙሉ ትከሻዎቻችንን አንድ በማድረግ አብረን ስለ ወንጌል ሀይማኖት እንድንጋደል ጥሪ አደረግሁ፡፡ ይህ መከራችንን ያቀልልናል÷ ያሳምረዋል÷ እንዲሁም ፍሬያማ ያደርገዋል፡፡ ምልክት ይሆናል፡፡ ጸልዩልን፡፡ ስራችንን እንወደዋለን፡፡ ስለ እናንተ መልካም÷ ስለ ክርስቶስ ክብር ይበልጡን ለማድረግ ቃል እንገባለን፡፡

*መጋቢ ጆን ፓይፐር ለመጋቢዎች በሙሉ፡፡*